በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡

የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፤

<u>ከዲኑ ፡ የተሰጠ ፡ መግለጫ ።</u>

፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፲፱፻፷፮/፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ ፡)

ይህ ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲንነት ፡ የምሰጠው ፡ የመጨረሻ ፡ መግለጫዬ ፡ ሌሎች ፡ ከባድ ፡ ሥራዎች ፡ ስላመዘኑ ፡ የተጻፈው ፡ በችኮላ ፡ ነው ። በሥራ ፡ በተመሉት ፡ ባለፉት ፡ አራት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የእኔ ፡ ኑሮ ፡ የጋራ ፡ ጥረት ፡ ውጤት ፡ ከሆነው ፡ ከሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ በብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ የተሳሰረ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ መግለጫውን ፡ የጻፍሁት ፡ በታላቅ ፡ ስሜት ፡ ነው ። ይህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ወደፊት ፡ በጣም ፡ ትዝ ፡ ይለኛል ።

ዛሬ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤታችን ፡

ከ፫፻ ፡ በላይ ፡ የሚሆኑ ፡ የአራት ፡ ዓመት ፡ የዲግሪ ፡ ፕሮግራም ፡ ተማሪዎች ፡ ሲኖሩት ፡ በሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ ሲቋቋም ፡ የተማሪዎቹ ፡ ቍጥር ፡ እስከ ፡ ፭፻ ፡ እንደሚደርስ ፡ ይታመናል ።

በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ፴ ፡ የሕግ ፡ ዲግሪ ፡ ያላቸውና ፡ ፹ ፡ የሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ ያላቸው ፡ "የቀድሞ" ፡ ተማሪዎች ፡ ይኖሩታል ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ፫፻ ፡ የሕግ ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶችን ፡ መስጠቱ ፡ የሚታወስ ፡ ነው ፡ (የምስክር ፡ ወረቀቱ ፡ ፕሮግራም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ላሉት ፡ የሕግ ፡ ሰዎች ፡ ለዳኞችና ፡ ለፓርላማ ፡ አባሎች ፡ የተዘጋጀ ፡ መሠረታዊ ፡ የማለማመጃ ፡ ኮርስ ፡ ነበር) ፤

፫፻ ፡ የሚሆኑ ፡ በአማርኛ ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ትምህርታቸውን ፡ የሚከታተሉ ፡ የሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ ተማሪዎችና ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ (በአማርኛ) ፡ ለማግኘት ፡ የሚማሩ ፡ ፬፻፺ ፡ የሚሆኑ ፡ ተማሪዎች ፡ አሉት ፤ ከነዚህ ፡ ተማሪዎች ፡ አብዛኞቹ ፡ ዳኞች ፡ የፓርላማ ፡ አባሎች ፡ የመንግሥት ፡ ነገረፈጆች ፡ የፖሊስ ፡ መኰንኖችና ፡ የሥራ ፡ ፈቃድ ፡ ያላቸው ፡ ጠበቆች ፡ ናቸው ፤ በዚህ ፡ የንሚስ ፡ ጊዜ ፡ ፕሮግራም ፡ ውስጥ ፡ ፶ ፡ የሚሆኑ ፡ ዳኞች ፡ ከ፲ ፡ በላይ ፡ የሚሆኑ ፡ የፓርላማ ፡ አባሎችና ፡ ከ፹፫ ፡ በላይ ፡ የሚሆኑ ፡ የፖሊስ ፡ መኰንኖች ፡ አሉት ።

በአስመራና ፡ በሐረር ፡ የማታ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራሞችን ፡ ለዳኞች ፡ ለጠበቆችና ፡ ለፖሊሶች ፡ አቋቁሟል ፤ እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ተመሳሳይ ፡ ፕሮግራም ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በጂማ ፡ ይጀመራል ፤ በሚቀጥለው ፡ የሐምሌ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ በአስመራ ፡ ከተማ ፡ በሚደረገው ፡ የምረቃ ፡ በዓል ፡ ፸ ፡ የሚሆኑ ፡ ዳኞች ፡ ሕግ ፡ አስከባሪዎችና ፡ ጠበቆች ፡ የምስክር ፡ ወረቀትና ፡ ዲፕሎማ ፡ ይቀበላሉ ፡

፲፰ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ መምህራንና ፡ ፲፩ ፡ የግማሽ ፡ ጊዜ ፡ መምህራን ፡ አሉት ። አሥር ፡ ሺህ ፡ መጻሕፍትን ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አለው ። በተጨማሪም ፡ ያልታተሙ ፡ ጽሑፎችን ፡ የሚያጠቃልልና ፡ ለወደፊቱ ፡ ምሁራን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድጋፍ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልበትን ፡ አንድ ፡ <u>የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መዝገቦች ፡ ክፍል</u> ፡ በቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ በማቋቋም ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

<u>የአፍሪቃ ፡ ሕግ ፡ መሻሻል ፡ በሰነድ ፡ መልክ ፡ የሚዘጋጅበትን</u> ፡ <u>አንድ ፡ ማእከላዊ ፡ አቋም</u> ፡ መስርቷል ። በማራቢያ ፡ መኪና ፡ የተባዛና ፡ የተጠረዘ ፡ ለ፲፩ ፡ መደበኛ ፡ የሕግ ፡ ትምህርቶች ፡ ማስተማሪያ ፡ የሚሆን ፡ ጽሑፍ ፡ አዘጋጅቷል ። ከ፻ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ጠቃሚ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮችና ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የተጻፉ ፡ ብዙ ፡ አንቀጾች ፡ የሚገኙበትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ አሳትሟል ። የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ የሚመለከቱ ፡ ስምንት ፡ መጽሐፎች ፡ አሳትሟል ። ሁለት ፡ ተጨማሪ ፡ መጻሕፍት ፡ በማተሚያ ፡ ቤት ፡ ይገኛሉ ።

<u>የተጠቃለሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጎችን</u> ፡ (ከጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ በመተባበር) ፡ ለማሳተም ፡ አቅዷል ። አንድ ፡ <u>የሕግ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ በአማርኛ ፡ በእንግሊዝኛና ፡ በፈረንሳይኛ</u> ፡ ቋንቋዎች ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። የኢትዮጵያን ፡ ጥንታዊ ፡ ፍርዶች ፡ የያዘውን ፡ ጽሑፍ ፡ (ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ የተሰጡና ፡ አዲስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ሕግ ፡ የሚያሳዩ ፡ ፍርዶች) ፡ በመተርጐምና ፡ በማራቢያ ፡ መኪና ፡ በማባዛት ፡ ላይ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ምንጭ ፡ የሆነውን ፡ <u>ፍትሐ ፡ ነገሥትን</u> ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ተርጉሞ ፡ ለማሳተም ፡ እርምጃ ፡ ወስዷል ።

በጣም ፡ የተቸገሩ ፡ ተማሪዎች ፡ የሚኖሩበት ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ቤት ፡ ለማሠራት ፡ ፹፪ሺህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ከግል ፡ በጐ ፡ አድራጊዎች ፡ ሰብስቧል ።

ብዙ ፡ ከሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ የተዋጡ ፡ ፕሮግራሞችን ፡ እናንተው ፡ ፍረዱ ፡ የተባለውን ፡ የቴሌቪዥን ፡ ፕሮግራም ፡ ጭምር ፡ ያዘጋጀ ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ አለው ።

የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤትን ፡ መንፈስ ፡ የሚያጠነክርና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለሕግ ፡ ለሕግ ፡ ትምህርትና ፡ ለሕግ ፡ ሙያ ፡ እድገት ፡ ከፍተኛ ፡ ድጋፍ ፡ ይሰጣል ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልበት ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበርን ፡ በማቋቋም ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ይመስለኛል ።

ከላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ እርምጃዎች ፡ የዲኑ ፡ ሥራ ፡ ቃላል ፡ አስዳሳችና ፡ ፍሬያማ ፡ እንዲሆን ፡ የረዱትን ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቼ ፡ የሆኑትን ፡ መምህራን ፡ እቅድ ፡ አወጣጥና ፡ የአንድነት ፡ መንፈስ ፡ አጉልተው ፡ ያሳያሉ ። እነዚህ ፡ እርምጃዎች ፡ በተጨማሪ ፡ ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የሕግ ፡ ባሕል ፡ መልክ ፡ በመስጠት ፡ <u>የሕግ ፡ መጽሔቱን</u> ፡ በማዘጋጀት ፡ ብዙ ፡ ጠቃሚ ፡ ጽሑፎችን ፡ በመተርጐም ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ ፕሮግራሞችን ፡ በማካሄድ ፡ የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ የክብር ፡ ደንብ ፡ በመጠበቅና ፡ በማሻሻል ፡ እንዲሁም ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ኑሮ ፡ ጣእም ፡ እንዲኖረው ፡ በማድረግ ፡ የረዱትን ፡ የአያሌ ፡ ተማሪዎች ፡ ልፋት ፡ አጉልተው ፡ ያሳያሉ ።

በመጨረሻም ፡ እነዚህ ፡ ከላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ እርምጃዎች ፡ በገንዘብ ፡ የተረዱት ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ምንጮች ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፡ ያስፈልጋል ።

በመምህራን ፡ ደመወዝ ፡ በሕግ ፡ መጽሔቱ ፡ ማሳተሚያ ፡ በማስተማሪያ ፡ መማሪያዎችና ፡ በቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ እድገት ፡ በኩል ፡ የገንዘብ ፡ ዕርዳታ ፡ ላደረገልን ፡ ለፍርድ ፡ ድርጅት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ። ከአሜሪካ ፡ ከካናዳ ፡ ከቤልጂግ ፡ ከጀርመን ፡ ከታላቋ ፡ ብሪታንያና ፡ ከፈረንሳይ ፡ የዕርዳታ ፡ ድርጅቶች ፡ የመምህራንና ፡ የመጻሕፍት ፡ ዕርዳታ ፡ እንዳንዴም ፡ ሁለቱንም ፡ ዓይነት ፡ ዕርዳታ ፡ በአንድነት ፡ አግኝተናል ። የተደረጉልን ፡ ዕርዳታዎች ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ጠቅመውናል ።

## ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ከተፈጸሙት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ተግባሮች ፤

## የሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ክለሳ ፤ የትምህርት ፡ ደረጃዎች ።

ከፍተኛ ፡ ኃላፊነት ፡ የተጣለባቸው ፡ እኛ ፡ ባለንበት ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ መምህራን ፡ ምን ፡ እናስተምር ፡ በሚለው ፡ ጥያቄ ፡ እንደሚጨነቁበት ፡ የሚታወቅ ፡ ነው ። በሕግ ፡ መምህርነት ፡ በቆየሁባቸው ፡ ፲፩ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ አዳዲስ ፡ ሐሳቦች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ፈጣን ፡ ለውጥን ፡ ለማስከተል ፡ አንዳንዶቹም ፡ የነበሩትን ፡ ሐሳቦች ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሳይወጡ ፡ ያለፈ ፡ ዓመት ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርትን ፡ ማዘጋጀትና ፡ ማሻሻል ፡ እኔ ፡ እንደምገምተው ፡ በአሜሪካን ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ካጋጠመኝ ፡ ተመሳሳይ ፡ ሥራ ፡ በይበልጥ ፡ የሚያስደስትና ፡ የሚያስቸግርም ፡ ነው ። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሌላው ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ አለን ፤ ተመሳሳይ ፡ የሌላቸው ፡ የማስተማር ፡ ችግሮችም ፡ አሉን ። በሕግ ፡ ሙያ ፡ የሠለጠኑ ፡ ሰዎች ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ሲሆኑ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ በአያሌ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ያላቸው ፡ ተፈላጊነት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። የፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ (አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ በመኖሪያ ፡ ቤቴ ፡ ከመጨረሻ ፡ ዓመትና ፡ ከሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ተማሪዎች ፡ ጋር ፡ ባደረጉት ፡ ውይይት) ፡ መሥሪያ ፡ ቤታቸውና ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ለሚመጡት ፡ አያሌ ፡ ዓመታት ፡ ብቁ ፡ የሆኑ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተመራቂዎችን ፡ ሁሉ ፡ ለመቅጠር ፡ መቻላቸውን ፡ አረጋግጠዋል ። ሌሎች ፡ ሚኒስትሮችና ፡ የመንግሥት፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችም ፡ በሕግ ፡ ለሠለጠኑ ፡ ሰዎች ፡ ያላቸውን ፡ ፍላጐት ፡ ገልጸውልናል ። በተጨማሪም ፡ አዳዲስ ፡ የአስተዳደር ፡ እቋሞች ፡ ለምሳሌ ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ መሻሻል ፡ የአውራጃ ፡ አስተዳደር ፡ የልማት ፡ ባንክ ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ፕሮግራም ፡ ሲቋቋሙና ፡ ሲሻሻሉ ፡ የት/ቤታችን ፡ ተመራቂዎች ፡ ተፈላጊነት ፡ እያደገ ፡ ይሄዳል ። በሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ረገድ ፡ ቀደምትነቱ ፡ አነስተኛ ፡ ቢሆንም ፡ በግል ፡ ሥራዎች ፡ ለሕግ ፡ ተመራቂዎች ፡ ብዙ ፡ ቦታ ፡ አለ ። ለተራው ፡ ዜጋ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ አገልግሎት ፡ የማቅረቡም ፡ ተግባር ፡ ለወደፊቱ ፡ በጣም ፡ ሊታሰብበት ፡ የሚገባ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።

ሥርዓተ ፡ ትምህርትን ፡ የሚያዘጋጅ ፡ ሰው ፡ የሕግ ፡ ሰው ፡ በምን ፡ በምን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ እንደሚችልና ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጥበትን ፡ ምክንያት ፡ ማወቅና ፡ ማመዛዘን ፡ አለበት ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ለማድረግ ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ በሌሎችም ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ለሕግ ፡ ሰዎች ፡ ያሉትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍት ፡ የሥራ ፡ ቦታዎች ፡ በሚያስረዳ ፡ ስሌት ፡ መሠረት ፡ ግምት ፡ መስጠት ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ መስሎ ፡ አይታየኝም ። እርግጥ ፡ ነው ፡ ብዙዎቹ ፡ የትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ተመራቂዎች ፡ ወደፊት ፡ በምን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንደሚውሉ ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በተጨማሪ ፡

በሕግ ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ለማመዛዘን ፡ ይበልጥ ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ማወቅና ፡ ማመዛዘን ፡ ያስፈልጋል ። በዚህ ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ለተደረገው ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ መምህራን ፡ ጉባኤ ፡ በተዘጋጀው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚከተለውን ፡ ሐሳብ ፡ ለመግለጽ ፡ ሞክሬ ፡ ነበር ።

በፓርላማ ፡ መሻሻል ፡ ሊፈጸም ፡ የሚችል ፡ ፕላን ፡ በማዘጋጀት ፡ በመሬት ፡ ሥሪት ፡ መሻሻል ፡ በአውራጃ ፡ አስተዳደር ፡ በማኅበራዊ ፡ የሥራ ፡ ፕሮግራሞች ፡ በሕዝብ ፡ ኩባንያዎች ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ያሉትን ፡ የተዛቡ ፡ አድራጎቶች ፡ በማረም ፡ የፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ድርጅት ፡ በማጠንከርና ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ረገድ ፡ አዳዲስ ፡ አቋሞችን ፡ ለመፍጠር ፡ በሚደረገው ፡ ጥረት ፡ የሕግ ፡ ሰው ፡ የመሪነቱን ፡ ሥፍራ ፡ እንዲይዝ ፡ ካልተገፋፋ ፡ በኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ ውስጥ ፡ በምን ፡ በኩል ፡ ፈጣን ፡ ለውጥ ፡ ለማድረግ ፡ እንደሚቻልና ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ጉዳት ፡ ሳይደርስ ፡ ለውጥ ፡ ለማምጣት ፡ እንዴት ፡ እንደሚቻል ፡ ስለነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ የሕግ ፡ ሰው ፡ ግልጽና ፡ እርግጠኛ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ እንዲያስብ ፡ ካልተማረ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሊደረግ ፡ ካልቻለ ፡ ግዳጃችንን ፡ በሚገባ ፡ ለመፈጸም ፡ የምንችል ፡ አይመስለኝም ።

በተጨማሪም ፡ የእድገት ፡ ዓላማዎች ፡ የኢኮኖሚ ፡ ግቦችን ፡ ለማግኘት ፡ የታቀዱ ፡ መሆን ፡ ቢገባቸውም ፡ ለዘለቄታ ፡ የሚፈለገው ፡ በጠቅላላው ፡ ብቁ ፡ የሆነ ፡ ኑሮ ፡ ስለሆነ ፡ በመሠረቱ ፡ ስለ ፡ መልካምነት ፡ ፍትሐ ፡ ነጻነትና ፡ የበለጸገ ፡ ኅብረተሰብ ፡ ልንጠበብ ፡ ይገባናል ፡ ብዬ ፡ አምናለሁ ።

በየአገሩ ፡ በተለይም ፡ አዲሱ ፡ ትውልድ ፡ በቁጣ ፡ በተመላበትና ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ በማይደሰትበት ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ሕጉ ፡ ለጥሩ ፡ ግብ ፡ በማያገለ ወደም ፡ የማያገለግል ፡ መስሎ ፡ በሚታይበት ፡ ቦታ ፡ በሕግ ፡ ላይ ፡ ነቀፋ ፡ መሠንዘሩንም ፡ አምናለሁ ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በየአገሩ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላሉ ፡ ተብሎ ፡ የሚታመነውን ፡ ከሀብት ፡ የሚገኘውን ፡ ምቾት ፡ ላላገኙ ፡ ሕዝቦች ፡ አዲስ ፡ የኑሮ ፡ ጐዳና ፡ የመክፈቱ ፡ ተግባር ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ለችግሩ ፡ ሁሉ ፡ መፍትሔ ፡ የፈጠረ ፡ የሚመስል ፡ ተራ ፡ ንግግርና ፡ በደፈናው ፡ የተደረሱ ፡ ጽሑፎች ፡ ቢኖሩም ፡ ከማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ ሊታሰብበትና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ሊጣርበት ፡ የሚገባ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። የአስቸኳይነት ፡ ስሜት ፡ ለዚህ ፡ ተግባር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የተስፋን ፡ የመተማመንና ፡ የመስዋዕትነትን ፡ ስሜት ፡ ይፈጥራል ። አንድ ፡ ታዳጊ ፡ በሆነ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ “የፈጣን ፡ ለውጥ ፡ ስሜት” ፡ ያላቸውን ፡ ዜጐች ፡ አሠልጥኖ ፡ ማቅረብ ፡ ግዴታው ፡ መሆኑን ፡ አምናለሁ ፤ “የፈጣን ፡ ለውጥ ፡ ስሜት” ፡ ያላቸው ፡ ስል ፡ ቦምብ ፡ በመጣል ፡ ወይም ፡ በመበጥበጥ ፡ ሰልፍ ፡ በማድረግና ፡ ምልክቶችን ፡ በመሸከም ፡ ሳይሆን ፡ (እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ተግባር ፡ ማከናወን ፡ እምብዛም ፡ አስቸጋሪ ፡ አይደለም) ፡ ይበልጥ ፡ አስቸጋሪ ፡ ይበልጥ ፡ ከባድ ፡ የሆነውን ፡ ማለት ፡ አዲስ ፡ ኅብረተሰብን ፡ የማቋቋም ፡ ሥራን ፡ ግዳጅ ፡ የሚወስዱ ፡ ማለቴ ፡ ነው ። ዩኒቨርሲቲው ፡ መርዳት ፡ ያለበት ፡ ግዳጃቸውን ፡ በስሜት ፡ ለማከናወን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከባድ ፡ የተለያዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባጋጠሙም ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ግዳጃቸውን ፡ የሚፈጽሙበትን ፡ ዘዴ ፡ ለማወቅ ፡ ስሜት ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ በማዘጋጀት ፡ ነው ። በታዳጊ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ብዙ ፡ ዩኒቨርሲቲዎች ፡ በነዚህ ፡ ተግባሮች ፡ ጥሩ ፡

ውጤት ፡ ማግኘታቸውን ፡ እጠራጠራለሁ ። እንዲያውም ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ ለማከናወን ፡ ያልቻሉ ፡ ይመስለኛል ፤ ይህ ፡ ከሆነበት ፡ ምክንያት ፡ አንዱ ፡ ሥራው ፡ የሚጠይቀውን ፡ የአእምሮ ፡ ዲሲፕሊን ፡ ሁኔታና ፡ ኃይል ፡ የሚፈጥሩ ፡ የሠለጠኑ ፡ ሰዎች ፡ ልምምድ ፡ ወይም ፡ በትምህርት ፡ ረገድ ፡ የመሬነቱን ፡ ሥፍራ ፡ የያዙ ፡ ሰዎች ፡ ስለሌሏቸው ፡ ነው ።

በጠቅላላው ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ የሚጸረሩ ፡ ዓላማዎች ፡ ያሉት ፡ ተግባር ፡ ያጋጠመን ፡ ይመስለኛል ። ባንድ ፡ በኩል ፡ በሕግ ፡ ሙያ ፡ የማሠልጠኑን ፡ ተግባር ፡ አጥብቀን ፡ መያዝ ፡ ይኖርብናል ። አሁን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በቂ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ዳኞች ፡ አማካሪዎች ፡ ጠበቆችና ፡ ሕግ ፡ አርቃቂዎች ፡ ይፈለጋሉ ፤ ጥቂቶች ፡ የትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ተመራቂዎች ፡ "ከሥራ ፡ ጋር ፡ የመለማመድ ፡ ፕሮግራም" ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ የመሠልጠን ፡ እድል ፡ ያጋጥማቸዋል ፤ በሌላው ፡ አገር ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ በግል ፡ በሚደረገው ፡ ሙያተኛ ፡ የመሆን ፡ ጥረት ፡ ውስጥ ፡ ይጠቃለላል ። ተመራቂዎቹ ፡ ራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ እንዲያሻሽሉና ፡ ከሥራ ፡ ጋር ፡ እንዲያለማምዱ ፡ ይገደዳሉ ፤ አዳዲስ ፡ ደረጃዎች ፡ እንዲፈጠሩ ፡ ከተፈለገ ፡ እነዚህን ፡ አዳዲስ ፡ የችሎታ ፡ ደረጃዎች ፡ ይመሠርታሉ ። እነዚህ ፡ ቁም ፡ ነገሮች ፡ ከባድ ፡ የሆኑ ፡ "ከሙያ" ፡ ጋር ፡ መተዋወቅንና ፡ ልምምድን ፡ ይጠይቃሉ ። ይህም ፡ ማለት ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሊፈጸሙ ፡ የሚችሉና ፡ በጽሕፈት ፡ የሚመለሱ ፡ ፕሮብሌሞች ፡ አሠራር ፡ የአነጋገር ፡ ስልት ፡ አጠናን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ የመከተል ፡ ልምድ ፡ መሰል ፡ የሕግ ፡ ሰነዶችን ፡ ማዘጋጀትና ፡ ተማሪዎቹ ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ መልመጃዎች ፡ እንዲሠሩ ፡ በጥብቅ ፡ መከታተል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ ተግባር ፡ ከባድ ፡ ነው ፡ መምህራኑ ፡ የተማሪዎቹን ፡ የትምህርት ፡ ችሎታና ፡ ፍላጐቶች ፡ እስኪያውቁ ፡ ድረስ ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ ይሆንባቸዋል ፤ ተማሪዎች ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጡ ፡ ዘዴ ፡ በጠቅላላው ፡ አዲስ ፡ ስለሚሆንባቸው ፡ በጣም ፡ ይችገራሉ ፤ ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ ተማሪዎቹ ፡ ወደ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከመምጣታቸው ፡ በፊት ፡ ከአስተማሪና ፡ ከመጻሕፍት ፡ ያገኙትን ፡ ብቻ ፡ መልሰው ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ የማስፈር ፡ ልምድ ፡ ስለነበራቸው ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ የመጀመሪያው ፡ ትምህርት ፡ ተማሪዎቹ ፡ ከተጨበጡ ፡ ነገሮች ፡ ጋር ፡ እንዲታገሉ ፡ ስላላስገደዳቸውና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎችን ፡ በአንድ ፡ ሐሳብ ፡ ሥር ፡ ማጠቃለልና ፡ የማይጨበጡ ፡ ሐሳቦችና ፡ አስተያየቶችን ፡ መስጠት ፡ የተጨበጡ ፡ መልሶችንና ፡ መፍትሔዎችን ፡ ከመስጠት ፡ ስለሚቀሉ ፡ ትምህርቱ ፡ ይከብዳቸዋል ።

ነገር ፡ ግን ፤ ለሙያ ፡ ጥበብ ፡ ብቻ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ መስጠት ፡ በቂ ፡ አይመስለኝም ። የዛሬው ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ተመራቂ ፡ በተለይም ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ በሚገኝ ፡ አገር ፡ በኅብረተሰቡ ፡ ውስጥ ፡ በእርግጥ ፡ "ምርጥ" ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ዋናው ፡ ጥያቄ ፡ ይህ ፡ ተመራቂ ፡ ሐሳብ ፡ በመስጠት ፡ በበጐ ፡ ተግባርና ፡ በመስዋዕትነት ፡ የኅብረተሰቡንና ፡ የአገሩን ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታዎች ፡ ለማሻሻል ፡ ይጥር ፡ ይሆን ፡ በምንስ ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ ፡ የሚለው ፡ ነው ። ይህም ፡ ጥያቄ ፡ ተመራቂው ፡ የቀሰመው ፡ ትምህርት ፡ ለዚህ ፡ ግብ ፡ ተብሎ ፡ መሰጠቱን ፡ ወይም ፡ ከእርግጠኛው ፡ ፍላጐት ፡ ጋር ፡ በጥልቀት ፡ ሳይዛመድ ፡ መሰጠቱን ፡ ሊገልጽ ፡ ይችላል ። ስለዚህ ፡ በማንኛውም ፡ ፋኩልቲ ፡ እንደሚደረገው ፡ ሁሉ ፡ ከማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ በላይ ፡ ሌላ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ መጨመር ፡ አለበት ። ሐሳብ ፡ አፍላቂነት ፡ አርቆ ፡ ማየትና ፡ ከታላቅ ፡ ግብ ፡ የመድረስ ፡ መንፈስ ፡ የማይገኙባቸው ፡ የማሠልጠኛ ፡ ዘዴዎች ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ናቸው ።

በዚህ ፡ ዓመት ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ከሚከተሉት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ግቦች ፡ ለመድረስ ፡ ተሻሽሎ ፡ ወጥቷል ።

፩ ፤ በሕግ ፡ ሙያ ፡ የልምምድ ፡ ማግኛው ፡ ዘመን ፡ ፩ ፡ ዓመት ፡ እንዲሆን ፡ ተወስኗል ፡ (ይኸውም ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ ጠቅላላ ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ትምህርት ፡ በኋላ ፡ ነው) ፤ ይህ ፡ የ፩ ፡ ዓመት ፡ የትምህርት ፡ ዘመን ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎት ፡ ስም ፡ ከመጨረሻው ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ለመንግሥት ፡ የሚደረገውን ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ አገልግሎት ፡ ይጨምራል ።

፪ ፤ ኅብረተሰብ ፡ ነክ ፡ ጥናቶች ፡ (ሶሻል ፡ ሳይንስ) ፡ እና ፡ ታሪክ ፡ በሥርዓተ፡ ትምህርቱ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገቡ ፡ ተደርጓል ።

፫ ፤ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ የሕግ ፡ ዘዴዎች ፡ ሥርዓት ፡ ያለው ፡ የፕሮብሌሞች ፡ አተናተንና ፡ ፍሬ ፡ ነገሮችን ፡ በሚገባ ፡ የመረዳት ፡ ዘዴዎች ፡ ቅድሚያ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ተወስኗል ።

፬ ፤ ፈረንሳይኛ ፡ አንድ ፡ አስፈላጊ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነት ፡ ሆኗል ፤ የዚህም ፡ ዓላማ ፡ ተማሪው ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሳለ ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ጽሑፎችን ፡ የማንበብና ፡ የመተርጐም ፡ በጽሑፎቹም ፡ የመጠቀም ፡ ችሎታ ፡ እንዲኖረው ፡ ነው ።

፭ ፤ የግለ ፡ ሰብ ፡ ሕግን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግን ፡ ሕገ ፡ መንግሥትንና ፡ የንግድ ፡ ሕግን ፡ የሚመለከቱ ፡ መሠረታዊ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ እንዲሰጡ ፡ ተወስኗል ።

፮ ፤ መጻፍ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ መታረምና ፡ ተደጋግሞ ፡ መጻፍ ፡ የሚገባቸውና ፡ ማርክ ፡ የሚሰጥባቸው ፡ የቤት ፡ ሥራዎች ፡ በየጊዜው ፡ እንዲሰጡ ፡ ተወስኖአል ፤ እነዚህም ፡ ተቀባይነት ፡ የሚያገኝ ፡ አንድ ፡ ከፍተኛ ፡ የጥናትና ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍን ፡ ይጨምራሉ ።

፯ ፤ ሕግ ፡ የማርቀቅና ፡ በሕግ ፡ ነክ ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ የመሳተፍ ፡ ልምምድ እንዲደረግ ፡ ተወስኗል ።

፰ ፤ የእድገት ፡ ፕሮግራሞችንና ፡ ሕግ ፡ ያልወጣባቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ እንዲሰጡ ፡ ተወስኗል ። ስለዚህ ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሻሻል ፡ የፖሊቲካ ፡ ባሕረ ፡ ሐሳብ ፡ (ቲዎሪ) ፤ የኢኮኖሚ ፡ ባሕረ ፡ ሐሳቦች ፡ የእድገት ፡ የፕላን ፡ የባላገር ፡ ልማትና ፡ የከተማ ፡ እድገት ፡ የመሬት ፡ ልማትና ፡ ሌሎችም ፡ ጉዳዮች ፡ በሚገባ ፡ ታስቦባቸዋል ። በተለይ ፡ በመጨረሻው ፡ ዓመት ፡ የትምህርት ፕሮግራም ፡ ውስጥ ፡ ለእነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ይሰጣቸዋል ።

"የትምህርት ፡ ደረጃዎች" ፡ ጉዳይ ፡ ትልቅ ፡ ግምት ፡ ሊሰጠው ፡ የሚገባ ፡ ነው ። በእኔ ፡ አስተያየት ፡ በአፍሪካ ፡ ዩኒቨርሲቲዎች ፡ የደረጃዎችን ፡ ጉዳይ ፡ ለማብራራት ፡ ታስበው ፡ በየጊዜው ፡ የሚሰነዘሩ ፡ አስተያየቶች ፡ ቢኖሩም ፡ ጉዳዩን ፡ በሚገባ ፡ ለይተው ፡ አይገልጹም ። የትምህርት ፡ ደረጃዎች ፡ የሌላው ፡ ሳይሆኑ ፡ የራሳችን ፡ የወደፊት ፡ ፍላጐቶች ፡ መግለጫ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ። የትምህርት ፡ ደረጃዎች ፡ ዝቅ ፡ የሚሉት ፡ መምህራኑ ፡ ከተማሪዎች ፡ የሚፈለጉ

ትን ፡ ሲያቀሉ ፡ ሲሰንፉና ፡ ሥራ ፡ ሲፈቱ ፡ ተማሪዎቹም ፡ እንደዚሁ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ሲፈቅዱላቸው ፡ ነው ። <u>የዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት</u> ፡ አሳሳቢ ፡ ተግባር ፡ ሊጠበቅ ፡ የሚችል ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ ማውጣትና ፡ ደረጃውንና ፡ ውጤቶቹን ፡ በየጊዜው ፡ መከለስ ፡ ነው ። ይህን ፡ ተግባር ፡ ለማከናወን ፡ ጥልቅ ፡ አስተዋይነት ፡ ያላቸውን ፡ የውጪ ፡ አማካሪዎችና ፡ ተመልካቾች ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በማስመጣት ፡ የፕሮግራሙን ፡ ቅርንጫፎች ፡ (ለምሳሌ ፡ የአንዱን ፡ የትምህርት ፡ ዓይነት ፡ ክፍል) ፡ ወይም ፡ ፕሮግራሙን ፡ በጠቅላላው ፡ እንዲመረምሩ ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል ፡ ይገባልም ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ የፕሮግራም ፡ ክለሳ ፡ የፈተና ፡ ወረቀቶችን ፡ መመርመር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ተማሪዎች ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡ መመልከትን ፡ ከተማሪዎቹና ፡ ከመምህራኑ ፡ ጋር ፡ መወያየትን ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፎችን ፡ ማየትንና ፡ አንድ ፡ መግለጫ ፡ ለዲኑና ፡ ለአካዳሚ ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ማቅረብን ፡ ጨምሯል ። እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከሚከተሉት ፡ ሊቃውንት ፡ የምክር ፡ እርዳታ ፡ የማግኘት ፡ ዕድል ፡ አጋጥሞታል ፡ የለንደን ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ የቀድሞው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ሲ ፡ ጋወር ፡ የቤልፋስት ፡ ኲዊንስ ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዊሊያም ፡ ትውኒንግ ፡ (ቀድሞ ፡ በዳሬሰላም ፡ ዩኑኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ፕሮፌሰር) ፡ የሃርቫርድ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሮጀር ፡ ፊሸር ፡ በሎስ ፡ አንጀለስ ፡ የሚገኘው ፡ የካሊፎርኒያ ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሙሬ ፡ ሹዋርትዝ ፡ የአዘን ፡ ፕሮባንስ ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዛቢር ፡ ብለን ፡ ዡቫን ።

<u>የገሚስ ፡ ጊዜው ፡ ፕሮግራም ፡ ክለሳ</u> ፡ የዲፕሎማና ፡ የሰርቲፊኬት ፡ ፕሮግራሞች ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ የሕግ ፡ ሥራ ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ መሠረታዊና ፡ ወዲያውኑ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የሚችል ፡ ትምህርት ፡ ለመስጠት ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ ቢቋቋሙም ፡ አብዛኛው ፡ የዚህ ፡ ፕሮግራም ፡ ትምህርት ፡ በአማርኛ ፡ መሰጠት ፡ ይገባዋል ። ይህን ፡ ትምህርት ፡ ከሚከታተሉት ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ የሥራ ፡ ልምምድ ፡ አላቸው ፤ ግን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ አልተማሩም ። አብዛኞቹ ፡ ተማሪውዎች ፡ ጊዜ ፡ ያጥራቸዋል ፤ አንዳንዶቹ ፡ ለሕጋዊ ፡ ሐሳብ ፡ አገላለጽ ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ነገሮች ፡ ያንሱዋቸዋል ። የሕግ ፡ ዲፕሎማዎችንና ፡ ሰርቲፊኬቶችን ፡ ተፈላጊውን ፡ ግብ ፡ በማያስገኝ ፡ መንገድ ፡ ለአያሌ ፡ ሰዎች ፡ ማሰራጨት ፡ ጉዳት ፡ ሊያመጣ ፡ ይችላል ።

እነዚህና ፡ ሌሎችም ፡ ጉዳዮች ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ በተደረጉት ፡ ብዙ ፡ የመምህራን ፡ ስብሰባዎች ፡ ላይ ፡ ተነስተው ፡ ብዙ ፡ ውሳኔዎች ፡ ተሰጥተውባቸዋል ፡ (፩) የሰርቲፊኬቱና ፡ የዲፕሎማው ፡ ፕሮግራሞች ፡ እንዲዋሀዱ ፡ ይኸም ፡ ማለት ፡ የሰርቲፊኬት ፡ ፕሮግራም ፡ የመጀመሪያና ፡ ወደ ፡ ዲፕሎማው ፡ ፕሮግራም ፡ ለሚገቡት ፡ ተማሪዎች ፡ የማጣሪያ ፡ ፕሮግራም ፡ እንዲሆን ፡ ፕሮግራሙ ፡ ለሁለት ፡ ዓመታት ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጥ ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መሠረታዊ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶችን ፡ ብቻ ፡ እንዲሸፍን ፡ ደረጃ ፡ በደረጃ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ የሕጐቹ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ክፍሎች ፡ እንዲጠኑ ፤ በሁለቱ ፡ ዓመታት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ተማሪዎቹ ፡ በውጤታቸው ፡ መሠረት ፡ (ቢበዛ) ፡ ከመቶ ፡ አምሳው ፡ ከበድ ፡ ወዳለው ፡ የዲፕሎማ ፡ ፕሮግራም ፡ እንዲገቡ ፡ ይፈቀድላቸዋል ። የዲፕሎማው ፡ ፕሮግራም ፡ ተማሪዎቹ ፡ በሰርቲፊኬቱ ፡ ፕሮግራም ፡ ውስጥ ፡ የሚሰጠውን ፡ ሕጐቹን ፡ የሚመለከት ፡ ትምህርት ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ እንደሚያውቁ ፡ በመቁጠር ፡ የሚሰጥ ፡ ሆኖ ፡ በነዚያ ፡ ሕጐች ፡ መሠረት ፡ ተጨባጭ ፡ የሆኑ ፡ የሕግ ፡ ፕሮብሌሞች ፡ መሥራትን ፡ ይጠይቃል ፤ የተማሪዎቹ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍላጐቶች ፡ እንዲረካ ፡ የትምህርት ፡

ዓይነቶችን ፡ የመምረጡ ፡ ዕድል ፡ የበለጠ ፡ ይሆናል ። ለምሳሌ ፡ ይህን ፡ ትምህርት ፡ የሚከታተሉ ፡ ከ፲፭ ፡ በላይ ፡ የሚሆኑ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ ከወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይልቅ ፡ ስለ ፡ ቀረጥ ፡ አሰባሰብ ፡ ማጥናትን ፡ ይመርጣሉ ፤ የፖሊስ ፡ መኰንኖች ፡ ምርጫ ፡ ግን ፡ የመጀመርያው ፡ ነው ። ተማሪዎቹ ፡ እንደየፍላጎታቸው ፡ ሲከፋፈሉና ፡ ለትንንሽ ፡ ጓዶች ፡ ትምህርት ፡ መስጠት ፡ ሲጀመር ፡ በፕሮግራሙ ፡ የመጨረሻ ፡ ደረጃዎች ፡ ላይ ፡ በጽሕፈት ፡ የሚመለሱ ፡ የሕግ ፡ ፕሮብሌሞችን ፡ በብዛት ፡ ማሠራት ፡ ያስፈልጋል ። ይህና ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፎችን ፡ ማዘጋጀት ፡ ጊዜን ፡ እንደሚጠይቅ ፡ ሁሉ ፡ እነዚህን ፡ ዓላማዎች ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋልም ፡ ጊዜን ፡ ይጠይቃል ። ነገር ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ እርምጃ ፡ ጠቃሚነት ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

## <u>የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እትሞች ።</u>

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ <u>የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት</u> ፡ ከሺህ ፡ በላይ ፡ የሚሆኑ ፡ አንባቢዎች ፡ አሉት ፤ ከ፻፻፺ ፡ በላይ ፡ የሚሆኑ ፡ ዳኞችና ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ የመጽሔቱ ፡ ጠባቂዎችና ፡ ደጋፊዎች ፡ ናቸው ። እነርሱም ፡ ሥራው ፡ እንዲቀጥልና ፡ እንዲስፋፋ ፡ ፳፭ ፡ ብር ፡ የደንበኞች ፡ ሒሳብ ፡ ይከፍላሉ ። በዚህ ፡ ዓመት ፡ መጽሔቱ ፡ በተቋቋመ ፡ በ፫ኛው ፡ ዓመት ፡ የመጀመሪያዎች ፡ የተማሪ ፡ አዘጋጆዎች ፡ የሥራ ፡ ውጤቶች ፡ ታይተዋል ። አንዳንድ ፡ የሁለተኛና ፡ የሦስተኛ ፡ ዓመት ፡ ተማሪዎች ፡ በመጽሔት ፡ ውስጥ ፡ ለማሳተም ፡ የየራሳቸውን ፡ የምርምርና ፡ የጥናት ፡ ጽሑፎች ፡ በማዘጋጀት ፡ ሠርተዋል ።

ይህ ፡ ሥራ ፡ በሕጉ ፡ ወይም ፡ በከፍተኛውና ፡ በጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፡ አንዳንድ ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆኑትን ፡ ጽንሰ ፡ ሐሳቦችን ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከቱትን ፡ በኦክስፎርድ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ የሚሰራጩ ፡ መጻሕፍት ፡ አሳትሟል ።

<u>ማቴሪያልስ ፡ ፎር ፡ ዘ ፡ ስተዲ ፡ እፍ ፡ ዘ ፡ ፒናል ፡ ሎው ፡ እፍ ፡ ኢትዮጵያ</u> ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ከሎውንስታይን ፡ የተዘጋጀ ፡ (አሁን ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ በመታተም ፡ ላይ ፡ ይገኛል) ።

<u>ኮንፍሊክት ፡ እፍ ፡ ሎውስ ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ</u> ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ከቤድሰር ፡ የተዘጋጀ ።

<u>አን ፡ ኢትዮፒያን ፡ ሊጋል ፡ ፎርም ፡ ቡክ</u> ፡ ከሪደን ፡ የተዘጋጀ ።

<u>ለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ መግቢያ</u> ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ከቫንዶርሊንደን ፡ የተዘጋጀ ።

<u>ላንድ ፡ ቻርተርስ ፡ ኢን ፡ ኖርዘርን ፡ ኢትዮፒያ</u> ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በሆንቲንፎርድ ፡ የተዘጋጀ ።

<u>ላንድ ፡ ቴኑር ፡ ኢን ፡ ቾሬ ፡ (ሸዋ ፡ ቾሮቪንስ) ፡ ኤ ፡ ፖይለት ፡ ፊልድስ ተዲ</u> ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ከማን ፡ የተዘጋጀ ።

<u>ዘ ፡ ሎው ፡ ሜኪንግ ፡ ፕሮሰስ ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ</u> ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ከሬደን ፡ የተዘጋጀ ።

ሰቴት ፡ ኤንድ ፡ ላንድ ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ከፓርንክረ ሰት ፡ የተዘጋጀ ።

ኢትዮጵያን ፡ ሲቪል ፡ ፕሮሲጀር ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ከሴድለር ፡ የተዘጋጀ ።

ኢትዮጵያን ፡ ኮንስቲቲውሽናል ፡ ሎው ፡ አንድ ፡ ዴቬሎፕሜንት ፡ ቴክስት ፡ ኤንድ ፡ ሊጋል ፡ ማቴሪያል ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ከፖልና ፡ ከክላፕሃም ፡ የተዘጋጀ ፡ (የሚታተምበት ፡ ጊዜ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡)

የተጠቃለሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጎችን ፡ ለማውጣት ፡ የተወጠነው ፡ ፕሮጄ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ በመሰብሰብ ፡ በመልክ ፡ በመ ልኩ ፡ አዘጋጅቶና ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ የወጡትን ፡ ማሻሻያዎች ፡ ሁሉ ፡ ጨምሮ ፡ ለማሳተም ፡ በመጣር ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። አብዛኞቹ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ሕጎች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ በሌሎችም ፡ ሕጎች ፡ ቢወጡም ፡ እንኳ ፡ በየጊዜው ፡ የሚወጡት ፡ አያሌ ፡ ሕጎች ፡ የሚገኙት ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ሕጎች ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ቻርተር ፡ እስከ ፡ ጉምሩክ ፡ ደን ቦችና ፡ ከሚኒስትሮች ፡ ሥልጣንና ፡ ሥራ ፡ ትእዛዝ ፡ እስከ ፡ የሕዝብ ፡ በአላትና ፡ የእሑድ ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ አዋጅ ፡ ያሉትን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚሸፍኑ ፡ ናቸው ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ባ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መርቀው ፡ ባቋቋሙት ፡ ነጋ ሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አማካይነት ፡ ሕጎቹ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በግልጽ ፡ ቢወጡም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ከወጡት ፡ አያሌ ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ ሕጎች ፡ መለየት ፡ አድካሚ ፡ ሥራ ፡ ሆኗል ። የጉምሩኮች ፡ የገቢና ፡ የወጪ ፡ ዕቃ ፡ ቀረጥ ፡ ማስከፈያ ፡ ደንቦች ፡ የዚህ ፡ ምሳሌ ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ታትመው ፡ የወጡት ፡ ባ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ከ፳፰ ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ ተሻሽለዋል ። ዛሬ ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃዎች ፡ የተመደ ቡትን ፡ የቀረጥ ፡ ልኮች ፡ ለማወቅ ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ የመጀመሪያውን ፡ ሠንጠ ረዥና ፡ እያንዳንዱን ፡ የተሻሻለ ፡ ደንብ ፡ መመርመር ፡ አለበት ። ተሻሽለው ፡ የወ ጡትን ፡ ደንቦች ፡ የሚያሳይ ፡ ዝርዝር ፡ ስለሌላም ፡ ከ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወዲህ ፡ የወጣውን ፡ እያንዳንዱን ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ መመርመር ፡ ይኖርበታል ። ይህ ፡ ምሳሌ ፡ ሕጎችን ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ተከታትሎ ፡ ለመረዳት ፡ የሚፈልገውን ፡ ሰው ፡ ከሚያጋጥሙት ፡ ችግሮች ፡ አንዱን ፡ ብቻ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ።

የፐብሊክ ፡ አድምንስትሬሽን ፡ ኢንስቲትዩትና ፡ የጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለዚህ ፡ ችግር ፡ መፍትሔ ፡ ለማግኘት ፡ ሕጎች ፡ ተሰብስበው ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ እንዲታተሙ ፡ ከአያሌ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የመጀመ ሪያውን ፡ እርምጃ ፡ ወሰዱ ። ባ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የጥቢ ፡ ወራት ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ ወደሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተዛወረ ፤ ትምህርት ፡ ቤቱም ፡ ከጠቅላይ ፡ ሚኒስ ትሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ሥራውን ፡ በማካሄድ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

የተሰበሰበው ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማሻሻያዎችን ፡ በመልክ ፡ በመልኩ ፡ ከማ ቅረቡና ፡ የተሰረዙትን ፡ ሕጎችና ፡ ቍጥሮች ፡ ከማስቀረትም ፡ በላይ ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ለማጥናት ፡ ወይም ፡ የሕጉን ፡ የአመጣጥ ፡ ታሪክ ፡ ለማ ወቅ ፡ የሚፈልገውን ፡ ሰው ፡ ለመርዳት ፡ ሰፋ ፡ ያሉ ፡ የቃላት ፡ መምሪያና ፡ የማ ውጫ ፡ ሠንጠረዦችን ፡ ይዟል ። በተጨማሪም ፡ የሕጉን ፡ ታሪክ ፡ በሚገባ ፡ ለመከ

ታትል ፡ እንዲቻል ፡ ለእያንዳንዱ ፡ የማሻሻያ ፡ ምንጭ ፡ ማስታወሻዎች ፡ ይዘጋጃሉ ።

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈው ፡ የተሰበሰበው ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ተቃርቧል ። የአማርኛው ፡ ክፍል ፡ ሥራም ፡ ተጀምሯል ፤ ይህ ፡ ሥራ ፡ በሚቀጥለው ፡ የክረምት ፡ ዕረፍት ፡ ወቅት ፡ በአንድ ፡ ከፍተኛ ፡ ችሎታ ፡ ባለው ፡ የተከታዩ ፡ ዓመት ፡ የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ ተማሪ ፡ በሚመሩት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ በአስቸኳይ ፡ እንዲካሄድ ፡ ይደረጋል ። በመሠረቱ ፡ ብሔራዊ ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሕጎችን ፡ በሚይዘው ፡ በተሰበሰበው ፡ ሕግ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ የአዲስ ፡ አበባን ፡ ከተማ ፡ ብቻ ፡ የሚመለከቱ ፡ ሕጎችንና ፡ ደንቦችን ፡ የሚይዝ ፡ ጽሑፍ ፡ በቅርቡ ፡ ይታተማል ። የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ መታተም ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ ነዋሪዎች ፡ ከፍተኛ ፡ ጥቅም ፡ ከመስጠቱም ፡ በላይ ፡ ተለቅ ፡ ያለው ፡ የተሰበሰበው ፡ ሕግ ፡ ሲታተም ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉትን ፡ የማተሚያና ፡ ሌሎች ፡ ችግሮች ፡ አስቀድሞ ፡ ለማወቅ ፡ ይረዳል ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ የተገኙትን ፡ ችግሮች ፡ ዋናው ፡ ዝግጅት ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ ለማቃለል ፡ ወይም ፡ ጨርሶ ፡ ለማስወገድ ፡ ይቻላል ።

ጐብኚ ፡ መምህራንና ፡ ሌሎች ፡ የታወቁ ፡ እንግዶች ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ አያሌ ፡ እንግዶች ፡ ባደረግንላቸው ፡ ጥሪ ፡ መሠረት ፡ ለአንድ ፡ ሳምንት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ጊዜ ፡ ጐብኝተውናል ። እያንዳንዱ ፡ የታወቀ ፡ ጐብኚ ፡ እዚህ ፡ በቆየበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ ንግግር ፡ ከማድረጉም ፡ በላይ ፡ በክፍል ፡ ውስጥ ፡ እየተገኘ ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጡን ፡ ዘዴ ፡ ተመልክቷል ። እነዚህም ፡ እንግዶች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከቱት ፡ ናቸው ፡—

ፕሮፌሰር ፡ ኖርማን ፡ አንደርሰን ፡ በለንደን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ከፍተኛ ፡ የሕግ ፡ ጥናቶችን ፡ እንስቲትዩት ፡ ዲሬክተር ፡ የእስላም ፡ ሕግ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ንግግር አድርገዋል ።

ፕሮፌሰር ፡ ጀርዚ ፡ ሮብሉስኪ ፡ በፖላንድ ፡ የሎድ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የትምህርት ፡ ክፍል ፡ ምክትል ፡ አስተዳዳሪ ፡ የሶሻሊስት ፡ ሕግና ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በፖላንድ ፡ በሚሉ ፡ አርእስቶች ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ።

የኤዛን ፡ ፕሮባንስ ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዛቪር ፡ ቦን ፡ ዠቫን ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተናጋሪ ፡ አገሮች ፡ ስለሕግ ፡ መሰናዶዎች ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጉዳዮችና ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ መሻሻል ፡ በሚሉ ፡ አርእስቶች ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ።

ሚስተር ፡ ያሽ ፡ ፒ ፡ ጋይ ፡ በዳሬሰላም ፡ የምሥራቅ ፡ አፍሪቃ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተባባሪ ፡ ዲን ፡ በታንዛኒያ ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሻሻል ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ።

የፐይቱር ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ጂ ፡ ቲክሴር ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ በሚገኙት ፡ አገሮች ፡ ያሉ ፡ የቀረጥ ፡ ጉዳዮች ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ።

በተጨማሪም ፡ በዲንነት ፡ የኔን ፡ ቦታ ፡ የሚወስዱት ፡ የዩል ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ኩዊንቲን ፡ ጆንስተን ፡ ለሁለት ፡ ሳምንታት ፡ ጐብኝተውናል ። የትምህርት ፡ ቤታችን ፡ የቅርብ ፡ ወዳጅና ፡ በሎስ ፡ አንጀለስ ፡ የሚገኘው ፡ የካሊፎ

ርኒያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲን ፡ የሆኑት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሪቻርድ ፡ ማክስዌል ፡ ለአንድ ፡ ሳምንት ፡ ጐብኝተውናል ።

የኢትዮጵያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎት ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎት ፡ ፕሮግራም ፡ ተካፋዮች ፡ ሆነዋል ። በዚህ ፡ ዓመት ፡ የትምህርት ፡ ወቅት ፡ ስድስት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስር ፡ አገልግለዋል ። የተማሪዎቹ ፡ አገልግሎቶች ፡ ከብዙው ፡ በጥቂቱ ፡ የጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ አማካሪነት ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ረዳት ፡ ሕግ ፡ አስከባሪነትና ፡ በአስመራ ፡ የገሚስ ፡ ጊዜ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ አስተማሪነት ፡ ናቸው ። በሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ጥቂት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ በሌሎች ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ለምሳሌ ፡ የመሬት ፡ ይዞታና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴር ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያገለግላሉ ፡ ብለን ፡ ብናስብም ፡ አያሌ ፡ ተማሪዎች ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስር ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ይደረጋል ። አንድ ፡ ተማሪ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሙያ ፡ ማኅበሮች ፡ ኮንፌደራሲዮን ፡ ይሠራል ።

የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎት ፡ ግዳጃቸውን ፡ የሚፈጽሙበትን ፡ ጊዜ ፡ የሚመለከት ፡ አንድ ፡ ጠቃሚ ፡ ውሳኔ ፡ ተሰጥቷል ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ በፕሮግራሙ ፡ የሚካፈሉት ፡ የክፍል ፡ ትምህርታቸውን ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ነው ። የመምህራን ፡ ጉባኤው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎት ፡ ቀዋሚ ፡ ኮሚቴ ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ መምህራን ፡ ይህን ፡ ልማድና ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማውን ፡ ካጠኑ ፡ በኋላ ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ አገልግሎቱን ፡ ለመስጠት ፡ ለጊዜው ፡ ትምህርታቸውን ፡ እንደሚያቋርጡት ፡ ሌሎች ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ተማሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ከመጨረሻው ፡ የትምህርት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ ይጠቀማሉ ፡ ሲል ፡ ወስኗል ። ወደፊት ፡ ከአንድ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ ወቅት ፡ በኋላ ፡ የሕግ፡ ተማሪዎች ፡ የአገልግሎት ፡ ግዳጃቸውን ፡ የሚፈጽሙት ፡ ከመጨረሻው ፡ የትምህርት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ዓመት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

## ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ የአሁኑ ፡ ሁኔታው ።

### የመጽሐፍቱ ፡ ብዛት ፡

ሀ ፤ ፫ልዩሞች ፡ ፱ሺ፯፻፲፰ ።

ለ ፤ በየጊዜው ፡ የሚወጡ ፡ ተከታታይ ፡ ጽሑፎች ፡ ፪፻፯ ።

ሐ ፤ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ፪፳፫ ፡ መጻሕፍት ፡ ፫፻፳፱ ፡ መጻሕፍት ፡ ያልሆኑ ፡ ጽሑፎች ።

መ ፤ ከንሐሴ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ወዲህ ፡ የተጨመሩ ፡ ቦልዩሞች ፡ ሺ፫፻፯ ።

ሠ ፤ የመጽሔት ፡ ለውጦች ፡ ፳፪ ።

ረ ፤ ስጦታዎች ።

ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቦልዩሞች ፡ ፳፯ ፡

ስሚዞስንያን ፡ ፩ሺ፪፻ ፡

በነጻ ፡ የተቀበልናቸው ፡ ፪ ፡

ከፈረንሳይ ፡ ኤምባሲ ፡ የተቀበልናቸው ፡ ፩ሺ ፡ ኤፍ ፡

## የቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ሠራተኞች ።

፩ ፡ ላይብረሪያን ፡

፩ ፡ የግማሽ ፡ ጊዜ ፡ ካታሎገር ፡

፩ ፡ ጸሐፊ ፡

፪ ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ረዳቶች ፡

፪ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዋሻ ፡ ጸሐፊዎች ፡

## የቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ መስፋፋት ።

ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ በተፋጠነ ፡ እድገት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ፤ ለአንባቢዎችና ፡ ለመጻሕፍት ፡ ተጨማሪ ፡ ቦታ ፡ አስፈልጓል ። ቤተ ፡ መጻሕፍቱን ፡ የሚጠቀሙበት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎችና ፡ መምህራን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ የሌላው ፡ ፋኩልቲ ፡ ተማሪዎችና ፡ መምህራንም ፡ ጭምር ፡ መሆናቸውን ፡ ማስታወስ ፡ ይጠቅማል ። በተጨማሪም ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ኤምባሲዎች ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ድርጅቶች ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ይገለገሉበታል ። በሚቀጥሉት ፡ ጥቂት ፡ ዓመታት ፡ የመጻሕፍቱ ፡ ቊጥር ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ እንደሚል ፡ ይታመናል ፤ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ኤምባሲዎች ፡ ያሏቸው ፡ አገሮች ፡ አያሌ ፡ ሕጐችን ፡ የሕግ ፡ መግለጫዎችንና ፡ መጽሔቶችን ፡ እንደሚለግሱን ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በአፍሪቃ ፡ ኢኮኖሚክ ፡ ኮሚሽን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ያሉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕጐች ፡ ወደሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ እንዲዛወሩ ፡ ስምምነት ፡ በመደረግ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ እራሱ ፡ አሁን ፡ ባለው ፡ የመጻሕፍት ፡ አደራደር ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ችግርን ፡ ያስከትላል ። የአፍሪቃን ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ በሰነድ ፡ ለማዘጋጀት ፡ የተመሠረተው ፡ ማእከላዊ ፡ አቋም ፡ እየተደራጀ ፡ ሲሄድ ፡ ለጽሑፎቹና ፡ ለጽሑፎቹ ፡ አንባቢዎች ፡ ተጨማሪ ፡ ቦታ ፡ ያስፈልጋል ። ለጊዜው ፡ የሕንጻውን ፡ በረንዳዎችና ፡ በሕንጻው ፡ የጓሮ ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ቦታ ፡ በግድግዳ፡ በማጠር ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቱን ፡ ለማስፋፋት ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የሚጨመረው ፡ ቦታ ፡ ካለው ፡ ፍላጐት ፡ ጋር ፡ ሲመጣጠን ፡ አነስተኛ ፡ ነው። ሌላው ፡ ዘዴ ፡ ደግሞ ፡ ዝርግ ፡ በሆነው ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሕንጻ ፡ ጣራ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የማንበቢያ ፡ ቦታ ፡ ማቋቋም ፡ ነው ። እጣራው ፡ ላይ ፡ የሚሠራው ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ክፍል ፡ በቂ ፡ ጥንካሬ ፡ ካለው ፡ ለተወሰኑ ፡ መጻሕፍት ፡ መደርደሪያም ፡ ያገለግላል ። የጠቅላላው ፡ ችግር ፡ የወደፊት ፡ መፍትሔ ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍትን ፡ በአሁኑ ፡ ሕንጻ ፡ አቅራቢያ ፡ ማሠራት ፡ ነው ። አዲሱ ፡ ሕንጻ ፡ ሲሠራ ፡ የአሁኑ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ መማሪያ ፡ ክፍሎችና ፡ እንደ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶች ፡ ያገለግላል ። ይህ ፡ ፕሮግራም ፡ በሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ አጀንዳ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ማግኘት ፡ አለበት ።

የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ቤት ፡ ባለፈው ፡ መግለጫ፡ ውስጥ ፡ ለሕግ ፡ ሙያተኞች፡ መገናኛ ፡ ቦታና ፡ ለተማሪዎች ፡ መኖሪያ ፡ የሚሆን ፡ "የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ቤት" በአስቸኳይ ፡ እንደሚያስፈልገን ፡ በዝርዝር ፡ ተገልጿል ። ለቤቱ ፡ ማሠሪያ ፡ ፺ሺ ፡ ብር ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ የግል ፡ ምንጮች ፡ ለመሰብሰብ ፡ ማቀዳችንንም ፡ ገልጸናል ፤ ይህንንም ፡ አድርገናል ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መልካም ፡ ፈቃዳቸው ፡ ሆኖ ፡ የፕሮግራማችን ፡ የመጀመሪያ ፡ ደጋፊ ፡ ሆነዋል ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከንጉሣዊ ያን ፡ ቤተሰብ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ኤምባሲዎች ፡ ከንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡

የሕግ ፡ ሙያ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ከፕሮፌሰሮችና ፡ ከተማሪዎች ፡ እንዲሁም ፡ ከውጪ ፡
አገር ፡ ወዳጆች ፡ ዕርዳታ ፡ አግኝተናል ። ይህ ፡ በአፍሪቃ ፡ ውስጥ ፡ ተመሳሳይ ፡
የሌለው ፡ ራስን ፡ በራስ ፡ የመርዳት ፡ ፕሮገሮ ፡ የተቋቋመውና ፡ ከፍሬ ፡ የደረሰው ፡
በሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ብርታት ፡ ነው ። የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ ስላሳዩት ፡
ብልህነትና ፡ የመሪነት ፡ ተግባር ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ። የሌሎች ፡ ፋኩልቲ ፡
ተማሪዎች ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎችን ፡ አርአያነት ፡ ተከትለው ፡ ተመሳሳይ ፡ ፕሮግሮ
ምችን ፡ እንደሚጀምሩ ፡ ተስፋ ፡ አለን ። ሕንጻው ፡ የሚሠራው ፡ በሕንጻ ፡ ኮሌጅ ፡
ሲሆን ፡ ሥራው ፡ ባ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንደሚፈጸም ፡ ተስፋ ፡ አለን ። እንዳጋጣሚ ፡
ሆኖ ፡ የመሣሪያዎች ፡ ዋጋ ፡ መጨመርና ፡ ሕንጻው ፡ የሚሠራበትን ፡ ቦታ ፡ ማዘ
ጋጀት ፡ አንዳንድ ፡ ችግሮችን ፡ ፈጥረዋል ። የሚፈለገውን ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡
ለማግኘት ፡ የሚደረገው ፡ ጥረት ፡ እንደ ፡ ቀጠለ ፡ ነው ፤ ግን ፡ ወደ ፡ ግቡ ፡ ተቃር
በናል ። የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ቤት ፡ በሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ ቆሞ ፡ ይታያል ።

የትምህርት ፡ ዓመቱ ፡ በብዙ ፡ የተማሪ ፡ ፕሮግራሞች ፡ የተመላ ፡ ነበር ።
ከውጪ ፡ አገር ፡ ጐብኝዎች ፡ የንግግር ፡ ፕሮግራሞች ፡ አብዛኞቹ ፡ የተካሄዱት ፡
በሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ ነበር ። የንግግሮቹ ፡ አርእስት ፡ ከእስላም ፡ ሕግ ፡
እስከ ፡ ታንዛኒያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሻሻል ፡ የሚደርሱ ፡ ነበሩ ። ከሕዝብ ፡ ግን
ኙነት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ የሚካሄድና ፡ አንዳንድ ፡ የታወቁ ፡
ኢትዮጵያውያን ፡ ተጋብዘው ፡ "የዩኒበርሲቲ ፡ ንግግሮች" ፡ የሚያደርጉበት ፡
ፕሮግራም ፡ እንዲቋቋም ፡ ታቅዶ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እቅዱ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አል
ዋለም ። ወደፊት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንደሚውል ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።

አራተኛው ፡ ዓመታዊ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀን ፡ በአቶ ፡ ተፈራ ፡
ደግፌ ፡ የንግድ ፡ ባንክ ፡ ጠቅላይ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የእንግዳ ፡ ንግግር ፡ አድራ
ጊነት ፡ ተከብሯል ፤ ተማሪዎቹ ፡ አንድ ፡ የተሟላ ፡ የሥራ ፡ ክርክር ፡ አሳይተዋል ፡
ይህም ፡ በአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ክርክርና ፡ የይ
ግባኝ ፡ ክርክሩን ፡ የሚጨምር ፡ ነበር ። በዘንድሮው ፡ ተመልካቾች ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡
የሕግ ፡ ሙያ ፡ አባሎች ፡ ነበሩ ፤ የተመልካቾቹ ፡ ቍጥር ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ የማን
ኛውም ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በዓል ፡ ላይ ፡ ከተገኙት ፡ የእንግዶች ፡ ቍጥር ፡
በልጧል ። ፕሮግራሙ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነበር ፤ ለሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ አባ
ሎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ።

## ለወደፊቱ ፡ ያለን ፡ ተስፋ ፤

አዲስ ፡ ዲናችን ፡ ፕሮፌሰር ፡ ኩዊንቲን ፡ ጆንስቶን ፡ በሐምሌ ፡ ወር ፡ እዚህ ፡
ይደርሳሉ ። ፕሮፌሰሩ ፡ በዬል ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ በአፍሪቃና ፡ በሌላም ፡ ቦታ ፡ ለብዙ ፡
ዓመታት ፡ አስተምረዋል ። በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ትጋት ፡ አንድነትና ፡ የአ
እምሮ ፡ ብስለት ፡ የሚዳብሩበትን ፡ ዘዴዎች ፡ ይዘው ፡ እንደሚመጡ ፡ አውቃለሁ ።

በመስከረም ፡ ወር ፡ ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አንድ ፡
ባዶ ፡ "የሕግ ፡ ሕንጻ" ፡ መርቀው ፡ ከከፈቱ ፡ ወዲህ ፡ ረዥም ፡ መንገድ ፡ ሄደናል ።

ግን ፡ ብዙ ፡ የሚሠራ ፡ ነገር ፡ አለ ።

ካጋጠሙት ፡ ዋና ፡ ችግሮች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ፩) የበጀቱ ፡ ማደግ—ዩኒቨርሲ
ቲው ፡ ለትምህርት ፡ ቤታችን ፡ በያመቱ ፡ ፩፻ሺ ፡ ብር ፡ መመደብ ፡ አለበት ፡

(እንደሚመድብም ፡ እምናለሁ) ፤ በተጨማሪም ፡ ለመምህራን ፡ ምርጫና ፡ ለውጪ ፡ አገር ፡ ሠራተኞች ፡ ትራንስፖርት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ወጪ ፡ መስጠት ፡ ይኖርበታል ። ለሚከተሉት ፡ አያሌ ፡ ዓመታት ፡ የውጪ ፡ ዕርዳታ ፡ ያስፈልገናል ፤ ግን ፡ የዕርዳታው ፡ ፍላጐት ፡ በየጊዜው ፡ መቀነስ ፡ አለበት ። ፪) በአንድ ፡ የትምህርት ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛው ፡ ወጪ ፡ የሚደረገው ፡ ለመምህራን ፡ ነው ። የተማሪዎቹንም ፡ ችሎታ ፡ ከፍ ፡ ከሚያደርጉት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጉዳዮች ፡ አንዱ ፡ የአስተማሪዎች ፡ ጥረት ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ አብዛኞቹ ፡ መምህራን ፡ ወጣቶች ፡ ቢሆኑ ፡ በማንኛውም ፡ አህጉር ፡ ካሉት ፡ የከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ መምህራን ፡ ጋር ፡ ለማወዳደር ፡ መቻሌን ፡ በደስታ ፡ እገልጻለሁ ። አሁን ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የሆኑ ፡ መምህራን ፡ ያሉን ፡ ይመስለኛል ። መምህራኑን ፡ በተለይ ፡ ከፍተኛ ፡ ልምምድ ፡ ያላቸውን ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቹን ፡ የማቆየቱና ፡ የመለወጡ ፡ ጉዳይ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ይህ ፡ ችግር ፡ መፍትሔ ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችለው ፡ የማስተማሪያ ፡ ክፍለ ፡ ጊዜዎችን ፡ ቀለል ፡ በማድረግና ፡ ለምርምርና ፡ ጥናት ፡ ፈቃድ ፡ በመስጠት ፡ ነው ። እነዚህን ፡ የመሳሰሉት ፡ ዘዴዎች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥቶ ፡ እገልግሎት ፡ መስጠትን ፡ አስደሳችና ፡ ጠቃሚ ፡ ያደርጋሉ ። እነዚህን ፡ መሪ ፡ ሐሳቦች ፡ (ፖሊሲዎች) ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ በሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ ከፍተኛ ፡ ጥረት ፡ ይደረጋል ፤ የበለጠ ፡ የአዋቂዎች ፡ ዕርዳታም ፡ ይገኛል ። ሥራው ፡ "በሞላ ፡ በኢትዮጵያዊያን ፡ እንዲካሄድ ፡ ማድረጉ" ፡ የማያጠራጥር ፡ አሳሳቢ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ቀዋሚ ፡ መምህራንን ፡ ለመምረጥ ፡ የወጡት ፡ ደረጃዎችና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚገባቸው ፡ ናቸው ። አንድ ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ መምህር ፡ ከመሆኑ ፡ በፊት ፡ ኃላፊነት ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ በቂ ፡ የሕግ ፡ ሥራ ፡ ልምምድ ፡ ማድረግ ፡ እንዳለበት ፡ እምናለሁ ። የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ያለውን ፡ ጥብቅ ፡ ፕሮግራም ፡ ማላላት ፡ የለበትም ። እንዲያውም ፡ የአስተማሪም ፡ ሆነ ፡ የተማሪ ፡ ተግባር ፡ እየጠነከረ ፡ መሄድ ፡ አለበት ። ፫) የሕንጻ ፡ ጉዳይ ፡ በተለይ ፡ በቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ በኩል ፡ ያለን ፡ ፍላጐት ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ችግር ፡ ፈጥሯል ፡ በሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ ለእድገት ፡ እቅድ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ መስጠት ፡ ያስፈልጋል ።

አንድ ፡ የመቋቋሚያ ፡ ጊዜ ፡ አልፏል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ወደፍጹምነት ፡ ደረጃ ፡ የምናደርገው ፡ ጉዞ ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ግንኙነታችን ፡ መስፋፋትና ፡ በአፍሪቃ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ መዲና ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ማእከላዊ ፡ አካል ፡ ማደግ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሊታሰብባቸው ፡ የሚገባ ፡ ጉዳዮች ፡ ናቸው ። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ አእምሮን ፡ በማጐልመሱ ፡ አስደሳችነት ፡ አለው ፤ ለአገሪቷ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፤ በሌሎች ፡ ቦታዎችም ፡ ተፈላጊነት ፡ አለው ።

ይህ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲዳብርና ፡ ከፍተኛ ፡ እርምጃ ፡ እንዲያደርግ ፡ እመኛለሁ ።

## ብሕግ ፡ ት/ቤት ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተመርቀው ፡ የወጡ ፡ ተማሪዎች ፡ ዝርዝር ።

### የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ ያገኙ ።

አቶ ፡ አባቢያ ፡ አባጀቢር ፡
ክቡር ፡ አቶ ፡ አበራ ፡ ጀምበሬ ፡
አቶ ፡ አቢዩ ፡ ገለታ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ፀጋዬ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ብርሃኑ ፡ ባየህ ፡
ክቡር ፡ አቶ ፡ ቡልቻ ፡ ደመቅሳ ፡
አቶ ፡ ግርማ ፡ ታደሰ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ኃይሉ ፡ መኩንን ፡
አቶ ፡ እጅጉ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ካሣ ፡ በየነ ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ገብረማርያም ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ማሞ ፡ መዘምር ፡
አቶ ፡ መብራቱ ፡ ዮሐንስ ፡
አቶ ፡ መንገሻ ፡ ወርቅነህ ፡
ሻምበል ፡ መስፍን ፡ ገብረቃል ፡
አቶ ፡ ነቢዩ ፡ ልዑል ፡ ክፍሌ ፡
አቶ ፡ ነጋ ፡ ፋንታ ፡
አቶ ፡ ሠይፉ ፡ ፈለቀ ፡
ሻምበል ፡ ሺመልስ ፡ መታፈሪያ ፡
(በማዕርግ) ፡
አቶ ፡ ሺመልስ ፡ ሁሴን ፡
ሻለቃ ፡ ታደሰ ፡ አብዲ ፡
አቶ ፡ ተክሉ ፡ መኩንን ፡
ሻምበል ፡ ወንዳየን ፡ ምሕረቱ ፡
አቶ ፡ ወርቁ ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
ሻምበል ፡ ይልማ ፡ ግዛው ፡
አቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ህሩይ ፡
አቶ ፡ ዘርዐ ፡ ብሩክ ፡ አበራ ፡
ሻምበል ፡ ዘርዓይ ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡
አቶ ፡ ዘመን ፡ ካሣ ፡

### ዲፕሎማ ፡ ያገኙ ።

አቶ ፡ መስፍን ፡ ፋንታ ፡
አቶ ፡ መኩንን ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ ሙላቱ ፡ ልካሳ ፡
አቶ ፡ ምናሴ ፡ ደጉ ፡
አቶ ፡ ሠይፉ ፡ ፈይሣ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ አናጌ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ የተሻ ፡ ወርቅ ፡
አቶ ፡ ሳሙኤል ፡ ወርቅነህ ፡
ሚስተር ፡ አራኪል ፡ ሳካጂያን ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ተሰፋዬ ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ ሣህለ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ ክፈተው ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ሣህሉ ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ዓለሙ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ተሾመ ፡ በየነ ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ገ/ሥላሴ ፡
የሻምበል ፡ ታምሩ ፡ ኃይለ ፡ ገብርኤል ፡
የሻምበል ፡ ታዬ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ታዬ ፡ ወንድማገኘሁ ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ነጋሽ ፡ ተክለ ፡ ማርያም
አቶ ፡ አሰፋ ፡ በቀለ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አሰፋ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አበራ ፡ ጉበና ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ጸጋዬ ፡
አቶ ፡ አክሊሉ ፡ አጥላባቸው ፡
አቶ ፡ አክሊሉ ፡ ቤተ ፡ ማርያም ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ እርዳው ፡ ዳርጌ ፡
የሻምበል ፡ ካሣዬ ፡ ማንደፍሮህ ፡
አቶ ፡ ካሣዬ ፡ እደም ፡
የሻምበል ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፡ ገብረ ፡
ማርያም ፡
ሻሽራሻ ፡ ዘውዱ ፡ አቶሮ ፡
አቶ ፡ ደምሴ ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ዳምጠው ፡ ምኒልክ ፡
አቶ ፡ ጀማነህ ፡ መካሻ ፡
ሚስተር ፡ ጆዋኪም ፡ ማቶቩ ፡
አቶ ፡ ገብረየሱስ ፡ ኃይለማርያም ፡
አቶ ፡ ጉደታ ፡ ቡሩ ፡
የሻምበል ፡ ጌታሁን ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ግርማይ ፡ ዘወልደ ፡
አቶ ፡ ጸደቀ ፡ ተክሌ ።

## ዲፕሎማ ፡ ያገኙ ፡ (አስመራ) ።

አቶ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ደባስ ፡
አቶ ፡ ሐሚድ ፡ ዑስማን ፡ ኢድሪስ ፡
አቶ ፡ ሑሴን ፡ ፋራሕ ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ሐንኪል ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ኑር ፡ ቁስማላ ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ አሊ ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ኢብራሂም ፡ ሐንጋላይ ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ኢድሪስ ፡ ዑመር ፡
አቶ ፡ መዋእል ፡ መብራሀቱ ፡
አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ ካሕሳይ ፡
አቶ ፡ ሰይድ ፡ ከሊፋ ፡
አቶ ፡ ሳልሕ ፡ ሺፋ ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ ይሕደጎ ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ ፍስሐ ፡ ጽዮን ፡
አቶ ፡ በየነ ፡ አስፍሐ ፡
አቶ ፡ በየነ ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ በራኺ ፡ ክልክል ፡
አቶ ፡ ብርሃነ ፡ ክፍለማርያም ፡
አቶ ፡ ተስፋት ፡ ዘሚካኤል ፡
አቶ ፡ ተስፉ ፡ ጽዮን ፡ ኢያሱ ፡
አቶ ፡ ተክኤ ፡ ገብረክርስቶስ ፡
አቶ ፡ አርአያ ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ አፈወርቅ ፡ ጆርጅ ፡
አቶ ፡ ኢሳይያስ ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡
አቶ ፡ ኪሮስ ፡ ገብረሕይወት ፡
አቶ ፡ ካሕሳይ ፡ አስፍሐ ፡
አቶ ፡ ካሣሁን ፡ ደረሰ ፡
የሻምበል ፡ ክብረ ፡ አብ ፡ በርሄ ፡
አቶ ፡ ወልዱ ፡ በርሄ ፡
አቶ ፡ እቁባዝጊ ፡ አድከመ ፡
አቶ ፡ ገብረሚካኤል ፡ ብሥራት ፡
አቶ ፡ ገብረሥላሴ ፡ ገብረትንሣኤ ፡
አቶ ፡ ገብረትንሣኤ ፡ ወልደሥላሴ ፡
አቶ ፡ ጸሐየ ፡ ዮሐንስ ፡

## ሠርቲፊኬት ፡ ያገኙ ፡ (አስመራ) ።

አቶ ፡ ሐረገወይን ፡ ዘርአዮሐንስ ፡
አቶ ፡ ሞሐመድ ፡ ኑር ፡ አህመድ ፡
አቶ ፡ ረዘነ ፡ ተስፋዬ ፡
አቶ ፡ ርእሶም ፡ ገብረማርያም ፡
አቶ ፡ ሳልሕ ፡ ካራር ፡
አቶ ፡ ስዩም ፡ ነጋሲ ፡
አቶ ፡ ነጋሽ ፡ ደስታ ፡
ግራዝማች ፡ አርአያ ፡ ሐጐስ ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ አብዱሰላም ፡ ሙሳ ፡
አቶ ፡ አምደብርሃን ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ በርሄ ፡ ወልደሚካኤል ፡
አቶ ፡ በየነ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ በርሄ ፡
አቶ ፡ ኤፍሬም ፡ ዑቁባገብርኤል ፡
አቶ ፡ ኪዳነ ፡ ብርሃኔ ፡
አቶ ፡ ክፍለ ፡ ኪዳነ ፡
አቶ ፡ የማነ ፡ ተክለ ፡
አቶ ፡ ይመስገን ፡ ሐይለ ፡ ጊርዮጊስ ፡
አቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ኃይለ ፡
አቶ ፡ ደበሳይ ፡ ተስፉ ፡ ጋብር ፡
አቶ ፡ ፋሲል ፡ ዶምሳስ ፡